# ምክር ቤቱ 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን አካሄደ

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ጥቅምት 26 ቀን 2011 ዓ.ም በኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ በደማቅ ሥነ-ሥርዓት አካሄደ፡፡

በዚህ የሀገራዊ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ናቸው፡፡

ጠቅላላ ጉባዔው በምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የቀረበለትን የ2010በጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አድምጦ ውይይት የተካሄደ ሲሆን በተጨማሪም የምክር ቤቱ የ2010 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫና የኦዲት ሪፖርት፤ በምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ማሻሻያ እና በሌሎች አጀንዳዎች ላይ ውይይት ተካሂዷል፡፡

በዚህም በስራ ላይ ያለው መተዳደሪያ ደንብ እና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ በሚሻሻሉባቸው ዝርዝሮች ላይም ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡
በጉባዔ ላይ ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ እና ከሁሉም አባል ምክር ቤቶች እና ማኅበራት የተወከሉ ከ140 በላይ ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፡፡